# “አፈ ጮሌን ላለማመን አብነቱ
# ሀብታሙ አያሌው እና ልደቱ አያሌው ”

ግርማ በላይ

March 14, 2018

ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ ሊሆን ይችላል፡፡ “ምን አዲስ ነገር ላገኝ” ከሚል እሳቤም ይሆን ይሆናል፡፡ የሆነው ሆኖ ግን ዘመን-አመጣሽ የመልእክት ሣጥኔን(ኤሜይሌን) ለብዙ ጊዜ አላየሁትም ነበር፡፡ ዛሬ ስከፍተው ግን የሚያናድደኝን ነገር ቁጭ ብሎ አገኘሁት፡፡ “ምነው ባልከፈትኩት!” ብዬ ተናደድኩ፡፡ ግን ደግሞ እንኳንም ከፈትኩት፡፡ ትንሽ ልተንፍሳ! እስከመቼ ታፍኜ?




በተማሪነቴ ወቅት ርዕሳቸውን ከተመለከትኳቸው የተማሪዎች የሂስ ጽሑፎች አንደኛው ምንጊዜም አይረሳኝም፡፡ “ልብ-ወለድ ላለማንበብ አብነቱ ‹አወይ ድህነቴ ሚስቴን አስቀማኝ›ን ማንበብ” ይላል – የመጽሐፉ ርዕስ የተቀየረ፡፡ “የኔንም ርዕስ ከዚያ ነው የኮረጅኩት” ለማለት ነው በዘወርዋራ፡፡

*“የሀብታሙ አያሌው ቅጥፈትና የባዶ ቅል ጥሬ መንኳኳት ተምሳሌት” ግዛቸው ሽፈፈራው(ኢንጂነር)*

ኢንጅነር ግዛቸው ስለ ሣተናው ወጣት ፖለቲከኛ ሀብታሙ አያሌው የጻፉትን ይህን ዘለግ ያለ ጦማር በአንድ የድረገጽ ባለቤትና አዘጋጅ ተልኮልኝ አገኘሁትና አነበብኩት፡፡ ጽሑፉ በተለጠፈበት ወቅት ገረፍ ገረፍ አድርጌ ማንበቤን አስታውሳለሁ፡፡ ነገር ሲቆይ በደምብ ይገባል መሰለኝ አሁን ስደግመው ግን ይህ ጉዳይ አለመታደላችንን ባገዘፈ መልኩ በንዴት አንጨረጨረኝ፡፡ “አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል” እንዲሉ በየመድረኩ በስሜት እየተንደቀደቁ ስለሕዝብና ስለሀገር ነፃነት የሚጮሁ “ወገኖች” (በቂ ማስረጃ እስከማገኝ “ተኩላዎች” ማለት ባለመቻሌ ማዘኔን ተረዱልኝና) ውስጣቸው ሲታይ ምን ዓይነት ገመና እንደታቀፉ አንድ ተግባራዊ ምሣሌ ለማየት ይህን ጽሑፍ በጥልቀት ማንበብ ጠቃሚ ነው፡፡ ኢንጂነር ልክ እንደኔ አንድ እግራቸው በዚህኛው አንድ እግራቸው ደግሞ በዚያኛው ዓለም የሚገኝ እንደመሆኑ በሀብታሙ ላይ ያን ያህል ርቀት በመጓዝ ይህን የመሰለ አስደንጋጭ የሀሰት ወሬ ፈጥረው የልጁን “መልካም ስምና ዝና” ያጎድፋሉ ብዬ ለማመን በጣም ተቸግሬያለሁ፡፡ በሌላም በኩል እርሳቸውን ልክ እንደ መልአክ ንጹሕ እምንጹሓን አድርጌ መውሰድም እንደሌለብኝ አውቃለሁ፡፡ ሰው እንደመሆናቸው ሊያጠፉ ወይም ሊሳሳቱ ይችላሉ፡፡ ስህተታቸውን ካመኑና ይቅርታ ከጠየቁ ደግሞ በቀድሞ ስህተት ሲወቀሱ ሊኖሩ እንደማይገባ እረዳለሁ፡፡ ለማንኛውም ስለሀብታሙ በጻፉት ጉዳይ ላይ እርሳቸውን በአካል አግኝቼ ተጨማሪ መረጃ ባገኝ ደስ ባለኝ፡፡ ግን እርሳቸው በጻፉት ላይና በተመሳሳይ ሌሎች ጽሑፎች ላይ ተንተርሼ የጥቂት መሰል አጭበርባሪ የሁለት ዓለም ሰዎችን ቁንጽል ታሪክ ለማስታወስ ወደድኩ፡፡ ይህን ለማድረግ የደፈርኩት አካፋን አካፋ ካላሉት የሚያመጣው ዳፋ ልክ እንደኛው ሁኔታ ሁሉ ሀገርን ወደፊት ሳይሆን ወደኋላ እየጎተተ መቅኖ የሚያስቀረው ትልቁ ማኅበረሰብአዊ ነቀርሣ ይህ ዓይነቱ የዜጎች እስስታዊ ባህርይና ይህን መጥፎ ባህርያቸውን ለመግለጽ እኛ ሕዝቡ የምናሳየው ግዴለሽነት ወይም ይሉኝታ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው፡፡ በተረፈ የሀብታሙ ውስጣዊ ማንነት በመታወቁ እኔ ድምቡሎ አላገኝም፡፡ ሀገርና ወገን ግን ይጠቀማሉ፡፡

መተዋወቅ ጥሩ ነው፡፡ እንደመተዋወቅ ያለ ጠቃሚ ነገር የለም፡፡ ይሁዳ ክርስቶስን በመሳም አሳልፎ መስጠቱን እናውቃለን፡፡ ይህ ሰው ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ይልቅ በክርስቶስ ተመራጭ ነበር፡፡ ስለተመረጠም ነበር የግምጃ ቤት ኃላፊ የነበረውና ገንዘብና ማንኛውም ንብረት ሁሉ በርሱ ቁጥጥር ሥር እንዲውል የተደረገው፡፡ ሀብት ያሳሳል፡፡ ንብረት ያስጎመጃል፡፡ ገንዘብ ያባልጋል፤ የኅሊናንም ሚዛን አዛብቶ የኃጢአትና የወንጀል ጎተራ ያደርጋል፡፡ ስለዚህም ነው ይሁዳ ከክርስቶስ ፍቅርና የዘላለምም ክብር ወጥቶ ከጠባቡ የጽድቅ መንገድ ይልቅ በሰፊው የብልጭልጭ የኃጢአት መንገድ በመጓዝ በዚያች መናኛ 30 አላድ ጌታውን አሳልፎ ለአራጆቹ የሸጠው፡፡ እርሱ ይህን ካደረገ እነልደቱና ሀብታሙ በምን ጎናቸው ይችሉታል ይህን ከባድ

የሥጋ ፈተና? መፍረድ አስቸጋሪ ነው ወንድሞቼ፡፡ "ወልደህ ሳትጨርስ/ሳትጨርሽ..." የሚባል አባባል ደግሞ አሁን ትዝ አለኝ – (እንዲህ ያለ ግፍ አትናገር/አትናገሪ ለማለት ነው)፡፡

ብዙ መናገርም ሆነ መጻፍ አያስፈልግም፡፡ በአጭሩ ኢትዮጵያችን የሰው ድርቅ የመታት ዕድ-ቢስ ሆናለች፡፡ የምናምነው ይከዳናል፡፡ ሰዎችን ባስቀመጥናቸው አናገኛቸውም፡፡ ሌላው ቀርቶ የኛን መስቀል ተሸክመው ብዙ መከራና ስቃይ የተቀበሉ የሚመስሉን እንደሀብታሙ ያሉ ወጣቶች ያን ፍዳ ለመቀበል የፈቀዱት ድብቅ ዓላማ ስላላቸው መሆኑን ስንረዳ የመረገማችን ምሉዕ በኩልሄነት ይከሰትልንና አንዳንዶቻችንና ነገሩ የገባን የምንገባበትን እናጣለን፡፡ ብዙዎቻችን በንግግር ማማርና በሀሰትና በፈጠራ ታሪክ ተጋንኖ በተገነባ  ተክለ ሰውነት እንማረካለን፡፡ ከመማረካችንም የተነሣ ፈጣሪን እስከምንረሳ ድረስ በግለሰቦች ወደማመን እንደርሳለን፡፡ በዚህ ዓይነቱ አካሄዳችን ብዙ ተጎድተናል፡፡ ሀገራችንም ወደማትወጣው አዘቅት የገባችበት ዋናው ምክንያት በነዚህን መሰል የጭቃ ውስጥ እሾህ ዜጎች ነው፡፡ አጭበርባሪ ቁጭ በሉዎችም እኛ ሕዝቡም መቼ ልብ እንደምንገዛ አይገባኝም፡፡ እናሳዝናለን፡፡

አፈ ጮማዎች በንግግራቸው ሰውን ያነሆልላሉ፡፡ በዓለማችን ዙሪያ ብዙ አፈ ጮማዎች ነበሩ፤ አሁንም አሉ፤ ወደፊትም መኖራቸው አይቀርም፡፡ እነሱን አምኖ ገደል የገባውና አሁንም ድረስ እየገባ ያለው  ሕዝብ ደግሞ ቁሩ የትዬለሌ ነው፡፡

አንድ ወቅት በኔ በራሴ የደረሰ ነገር ላውጋችሁ፡፡ ወያኔ እንደገባች ሰሞን ነው፡፡ በዚያን ወቅት አካባቢ የጄኔራል ወርቁ ዘውዴ ዘበኛ የነበረና በኋላ ላይ ኑሮ ሲከብደው ወዳልተበላበት የሃይማኖቱ ዘርፍ በመግባት "ባህታዊ ገ/መስቀል" በሚል የክት ስም ሕዝብን "የሚቀፍል" አጭበርባሪ ተነስቶ ነበር፡፡ እንዲህ በአነጋገሬ "የባለግሁት"ና ይህን ወንበዴ በዚህ መልክ የገለጽኩት ያኔ ስለዚህ ወመኔ ሰውዬ ስል ከሰው ጋር የተጣላሁበትን ያለፈ ታሪክ ለማጣጣት ነው፡፡ እናላችሁ በርሱ ስብከት ክፉኛ ከመነደፌ የተነሣ ስለሰውዬው አጭበርባሪነትና አታላይነት ጓደኞቼ ሲናገሩ ስሰማ ከምር እጣላቸው ነበር፡፡ በውነቱ ብዙ ጊዜ ተጣልቻለሁ፡፡ አንድ ሰው በስሜት ሲታወር ምን ሊያደርግ እንደሚችል ይህ ትዝታዬ በግልጽ ያስታውሰኛል፡፡ ... እየቆዬ ሳጣራና ወደኋሊናየ ስመለስ ግን ያ ሁሉ ስለ "ባሕታዊ"ው ይነገር የነበረው ተዓምር ሁሉ ሆን ተብሎ በአጋፋሪዎቹ የሚተወን ትያትር እንደነበር ገባኝ፡፡ ስንቱን አታለለው መሰላችሁ! ሕዝባችን ደግሞ ለመታለል በጣም ምቹ ነው፤ መጠየቅንና መመራመርን እንደወንጀልና እንደኃጢአትም የሚቆጥር ዜጋ በሚበዛበት ሀገር ወንጀለኞችም ይበዛሉና በጣም እየተጎዳን ነው፤ በዚያ ላይ ሃይማታዊ አስተምህሮው "አትመራመር፤ ትቀሰፋለህ" የሚል ስለነበር ይህ ኢ-ክርስቶሳዊ ትምህርት ለአወናባጆች ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸው እስካሁን ዘልቋል – ክርስቶስ ግን ያለው "ሁሉን እዩ የሚበጃችሁን ያዙ" ነው – "ኩሎ አመክሩ ወዘሠናየ አፀንዑ" " እንዲል መጽሐፍ ቅዱሣዊ ብሂሉ፡፡ በነገራችን ላይ እያወቀም የሚታለል ሳይኖር አይቀርም፡፡ ያ ሰው አሁን አማርጦ ያገባትን ሴት ይዞ ቀጨኔ አካባቢ ልጆቹን እየፈለፈለ ይኖራል፡፡ ማንም ዝምቡን እሽ ያለው የለም፡፡ ጌታ ይገስጸው!

እርሱን መሰል ቁጭ በሉዎች በየሰበካው ሞልተዋል – ከጳጳስ እስከ ዲያቆን – ከልሂቅ እስከ ደቂቅ፡፡ ለመታለል ዝግጁ የሆኑ ገልቱ ምዕመናን ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ የሀገር ግንባታና የነፃነት ጎሕ መቅደድ የሚታሰበውና የሚታለመው እንግዲህ በዚህ ዓይነቱ ማኅበረሰብአዊ መቼት ነው፡፡ ይህንን ሕዝብ ልደቱንና ሀብታሙን የመሰሉ እሳተ መለኮቶች ይቅሩና ታምራት ገለታንና እህተ ማርያም ተብዬዋን የመሰሉ ከ 4 ኛና ከ 8 ኛ ክፍል ያልዘለለ ትምህርት ያላቸው ቁጭ በሉዎች እንኳ በቀላሉ ያሞኙታል፡፡ ተጨንቀናላ! በወያኔ ግፍና በኑሮ ጣጣው ሳቢያ ሰማይ ምድሩ ዞሮብናላ! እንዴ – እኔም እኮ እግዜርን ፈርቼ እንጂ ሀሙስና ቅዳሜ መጋረጃ ጣል ባደርግ ታምራት ገለታን አስከነዳ ነበር፤ ለብቻየ የምነዳው አንድ የግል "ቸርች" ባቋቁም እኮ እኮ ከጥበበ ወርቅየና ከታምራት ላይኔ በሚያስንቅ ሁኔታ "ሕዝበ ክርስቲያን"ን መግፈፍ እችል ነበር፤ "የጨነቀው እርጉዝ ያገባል" እንዲሉ የጨነቀውና የጠበበው ሁሉ እስራኤል ዳንሳን የመሰሉ የፋራ ሀሰተኛ ነቢያትን ቤተ አምልኮዎችንና የአባይ ጠንቋይ የአውሊያ ቤቶችን ሲያጣብብ ማምሸት ማደሩን ስንገነዘብ ነዳጅ ያለቀባትና ኮምፓስ የጠፋባት መርከብ ፊታችን ላይ ድቅን ልትልብን ትችላለች – ኢትዮጵያን ተመስላ፡፡ በዚህ ዘመን ጠንቋይና ቄስ ወይም ደብተራ መሆን በጣም ያበላል፡፡ የትንግርት ዘመን፡፡ ሰው እንዴት እየባሰበት ይሄዳል? ወደፊት መጓዝ ቢያቅተው እንዴት ያለውን  እንኳን ይዞ ሕይወትን መቀጠል አቃተው?

ካነበብኩት አንድ ነገር ላስታውስ፡፡ አንድ ራሱ በእግዚአብሔር የማያምን ሰው በቀን ሚሊዮኖችን በመስበክ የእግዚአብሔርን መኖር ያሳምን ነበር፡፡  በድራማውም ዓለም ብዙ ገጸ ባሕርያትን እናያለን – ያልሆኑትን ሆነውና መስለው ሲከውኑ፡፡ ይህ ዓይነቱ የማስመሰል ባሕርይ በነልደቱና ሀብታሙ ውስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡ እነዚህን መሰል ሰዎች የራሳቸው ማንነት የላቸውም፡፡ Simply put, they are vessels of some abstract being, most certainly, of devilish nature. ልደቱ ሲናገር እንዴት እንደሚያፈዝ እኔ በግል አውቃለሁ፡፡ ባሕርዩ ግን ሁላችንም በግልፅ እንደምናውቀው በገንዘብ ሊገዛ የሚችል 360 ዲግሪ ተጣጣፊ ሰው ነው፡፡ ይህንንም በምርጫ 97 ወቅት በሚገባ አሳይቷል (በአሁኑ ወቅት አክሱም ላይ ባለአራት ኮከብ ሆቴል አለው ይባላል)፡፡ እርሱን መሰል ፍጡራን ሥልጣን ወዳድ ናቸው፡፡ ዝና ያነፈልላቸዋል፡፡ የሀብት ፍቅር ያናውዛቸዋል፡፡ በቁም ሊለቀስላቸውና ተዝካር ሊወጣላቸው የሚገባቸው አሳዛኝ ስብዕና የተላበሱ ናቸው፡፡ ለሀብትና ለሥልጣን ሲሉ የማይገቡበት ጉድጓድ የለም፡፡ ደግሞም የማንም መጠቀሚያ ናቸው፡፡ Money can buy. ሴተኛ አዳሪ እንኳ አንዳንዴና ኪሷ ሞቅ ሲል የምትመርጠውና የምታንጓልለው ወንድ አለ – የማታስተናግደው፡፡ በነዚህ ሰዎች ዘንድ ግን መምረጥ ቃሉም አይታወቅም፡፡ የከፈለ ይጠቀምባቸዋል፡፡ በቀላሉ ስለሚያኮርፉም ከአንዱ ወደሌላው ለመሸጋገር የሚወስድባቸው ቅጽበት ከዐይን እርግብግቢት ሊያንስም ይችላል፡፡ ጥንቃቄን ይፈልጋሉ፡፡ እነዚህን ሰዎች ምሥጢረኛ ማድረግም አይቻልም፡፡  ከ"እኛ" ይልቅ "እኔ"ን የሚያበዙ ራስን በማምለክ የተጠመዱ በመሆናቸው ስለ ሃይማኖት ያላቸው ግንዛቤ እጅግ ደካማ ከመሆኑም

ባሻር እነሱን ወደ ሃይማኖት ለማጥመቅ ፈተናው ከባድ ነው:: ጉረኝነትና ስራስ መደስኮር ደግሞ ዋና መገለጫቸው ነው:: በሞቀበት ይዘፍናሉ:: የራሳቸው የሆነ አቋምም ሆነ የማንነት መገለጫ የላቸውም:: ይሉኝታቢስነትና ሀፍረትየለሽነት ልብሳቸው እንጂ የሚያፍሩባቸው አይደሉም:: የሚሸጥ ቢያጡ እናታቸውንና ሚስት ልጆቻቸውን እንዳወጡ ይቸበችባሉ:: ትዝብት ብሎ ነገር አያውቁም:: በንግግር ደፋሮች ናቸው:: ንግግራቸው ምን እንደሆነ ሳይሆን ምን ውጤት እንደሚያመጣ ብቻ ነው ዋና ትኩረታቸው:: ስለነዚህ ሰው መሳይ በሸንጎዎች ብዙ ማለት ይቻላል:: ግን ብዙዎቻችን ስለምናውቃቸው ከዚህ በላይ መድከም አያስፈልግም::

እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ውስጥ የሚከተሉትን በጉልኅ እናገኛለን:: እኔ ትዝ ያሉኝን አስቀመጥኩ:: እናንተ ደግሞ የምታውቋቸው ካሉ ተናገሩ:: አዎ፣ በግልጽ መነጋገር ነው:: የምንጠነስሰው ጠላ ሁሉ እየሾመጠረ ሀገርና ሕዝብ አጥተን የቀረነው በነዚህ ዓይነቶቹ ሞጭላፋ አሰለጦች በመሆን ለነሱ ማዘን በገዛ አንገት ላይ ገመድ እንደመጠምጠም ነው:: እነዚህ ሰዎች በጮሌ አፋቸው እንደሚወሽክቱት የሕዝብ ወገኖች ቢሆኑ ኖሮ – ለአብነት ያህል – ሀብታሙ አያሌው ይህን የመሰለ አስነዋሪ ስድብ በኢሜል በመላክ ባውለታውን አያስቀይምም ነበር::

"እኔን አናድዳለሁ ብለህ ኮምፒውተር ላይ ስትውል *ተጠናግሮ የሚያለቅሰው ሊይንህ እንዳይጠፋ። እኔ ንቄ ትቼሃለሁ ቅናት ያንገበገበህ ወራዳ መሆንህን ሁሉም ስለተረዳ ካልደከመህ ቀጥል።እኔ እንዳንተ ካለው እርባናቢስ ተጠናግሮ ከሚያክ ሰው ጋር ልመላለስ!* " (አፅንዖት የተጨመረ)

አንባቢ ይፍረደው:: በጊዜ የጮ ጅብ አያሳድረኝም ይሉ ነበር አባቶች:: ይህን መሰል ክርት ጠባይ ይዞ የሚቃዥርባት አራት ኪሎ ቤ መንግሥት ቢገባ በቲቪ መስኮት ብቅ ብሎ " እናንት ቅማላሞች የኢትዮጵያ ሕዝቦች … " እንደማይለን ምንም ዋስትና የለንም:: የጉድ ሀገር! ኧረ ክፍላችን ይቆጠርና የዘብር ወይም የሸንኮራ መሆኑም ዕጣ አውጥተን እንለይና ጠበል እንረጭ ግዴላችሁም::

ክርስቶስ ስለኔ ተገረፈ፤ ተሰቃዩ፤ ተሰቀለም:: ይሁንና በአንዱም የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ አልሰደበኝም:: እንዲያውም በተቃራኒው "የሚሰድቧችሁን መርቁ" ነው ያለው:: ስለዚህ የሕዝብ ወገን ለመሆን መታሰርና መገረፍ ብቻውን እንደማይበቃ ቢያንስ ከዚህ መጣጥፍ አንዳች ግንዛቤ ልንጨብጥ እንደሚገባን በታላቅነቴ ማስታወስ እፈልጋለሁ:: "ታላቅ ነኝ" የምለው በዕድሜና ምናልባትም በተሞክሮ እንጂ በሌላ አይደለም:: ሕዝብ የሚወደውንና የሚያከብረውን ይወዳል:: የሚያዋርደውንና የሚሰድበውን ግን ይጠላል::

1. ዶክተር ፕሮፌሰር ኢንጂነር ፊልድ ማርሻል የዓለም ሎሬት የኖቤል ተሸላሚ ልደቱ አያሌው – የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም፤ የቀይ መስቀል የበላይ ጠባቂ፤ የወቅቱ የአፍሪካ ኅብረት ሊ/መንበር፤ የተ.መ.ድ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ሰብሳቢ፣ የህክምና ሊቅ፣ የታሪክ ተመራማሪ፣ የፍልስፍና ሊቀ ሊቃውንት፣ የከርሰ ምድር አጥኚ፣ የሕዋ ተመራማሪ፣….
2. ዶክተር … ብርሃኑ ዳምጤ (አባ መላ) – የኢትዮጵያ የዕድሜ ልክ ፕሬዝደንት….(ከላይ ያለውን ለሁሉም ድገሙልኝ እባካችሁ!)
3. ፕሮፌሰር … ሀብታሙ አያሌው – የኢፌድሪ ጠ/ሚኒስትር፣ …
4. ዶክተር … አብርሃም ያዬህ …
5. ባህታዊ ገ/መስቀል – ርዕሰ ጳጳሣት ወፓትርያርክ ዘኢትዮያ፣ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክ ሃይማት፣ ርዕሳ ጳጳስ ዘአክሱም፣ የዓለም አብያተ ክርስቲን ጉባኤ አባል…
6. ሚዲያ የማያውቀንና በየመንደሩ ጁንታ መሆን የምንፈልግ ግልብ ዜጎች …

እኛ እንዲህ ነን እንግዲህ:: ከዚህ አስጠሊታ ዐውድ ካልወጣን ምኞታችን ህልም፤ ህልማችን ቅዠት እየሆነ ምንጊዜም የባለጌዎች መጫወቻ እንደሆን እንቀራለን:: ወያኔ ነገ ይሄዳል – ወይም ዛሬ ማታ:: ግን ጠባይና ምግባራችን በዚሁ መልክ ከቀጠለ በቁጥር እንጂ በግብር የማይለያዩ ወያኔዎችን ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስናገድን እንኖራለን:: ስለዚህ ውስጣችንን እንመርምር:: በጭፍንና በወረት አንመራ:: የሚጠቅመንን ከማይጠቅመን፣ እውነተኛን ከሀሰተኛ፣ ተኩላና ቀበሮን ከበግ የመለየት ዕውቀትና ችሎታ እናዳብር:: ባለንት መርገጥ ይብቃን:: ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳን::